# የመሃይምናን ትምህርት ብሔራዊ ጉባኤ

ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ. ም.
ያሳለፋቸው ልዩ ልዩ ውሳኔዎች ።

የመሃይምናንን ትምህርት ሁናቴ ለማጥናት ብሔራዊ ጉባኤ ከታኅሣሥ ፳፩ እስከ ፳፬ ድረስ በቀ. ኃ. ሥ. ዩ. ውስጥ ተደርጐ ነበር ። አዘጋጆቹም ብሔራዊ ፊደል ሠራዊት ፤ ቀ. ኃ. ሥ. ዩ. የትምህርት ክፍልና ትምህርት ሚኒስቴር ነበሩ ። የጉባኤው ዋና ውሳኔ በሚከተለው ቀርቦአል ።

—ሀ—

## የመሃይምናን ትምህርት ዓላማና ፍልስፍናው

፩/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማና ፍልስፍና እግቡ ለማድረስ ካሁን በፊት የተብራራ ድንጋጌ የለም ። የግል ጥረትና የበጎ ፈቃድ ብቻ አለመብቃቱን በመረዳት ፤ ለወደፊቱ ዓላማው በሕግ እንዲደገፍ ጉባኤው በቅ ድሚያ ያሳስባል ። በብሔራዊው የአምስት ዓመት ፕላንም የመሃይምናንን ትም ህርት እንደ ፕሮግራም ቀርቦአል ። ግን ወደፊት የሚማሩትን ብዛት ጠቅሶ ያልፋል እንጂ ፤ እንዴት ሥራ ላይ እንደሚውል በተለይ በጀትን አስይዞ ፤ መምሪያ አይሰጥም ። የመሃይምናን ትምህርት የሚመራበት ብሔራዊ ዓላማ መኖር እንዳለበት ጉባኤው ያስሳባል ።

፪/ ጉባኤው የተነሳሳበት ዋና ዓላማ የመሃይምናንን ትምህርት ይዞታ ለማሻሻል ነው ። መሃይምነትን ከመሠረቱ ለማጥፋት ከተፈለገ ዓይነተኛው መፍትሔ ፤ በትምህርት ቤት ዕድሜ ያሉትን በማስተማር ከፍ ያለ ጥረት ማድ ረግ ያስፈልጋል ።

፫/ የመሃይምናን ትምህርት የሚሰጠው ፤ ማወቅ ወይም ሁሉ ይማር የሚ ለው ፍልስፍና መብት መሆኑን በመረዳት ነው ።

፬/ አማርኛ ቋንቋን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አውቆ ፤ ብሔራዊ መገናኛ እንዲሆነው በማሰብ ለመሃይምናን የአማርኛ ትምህርት ይሰጣል ።

ከብሔራዊው ድርጅት በአማርኛ ለመሃይምናን የሚቀርቡት ጽሑፎች የግል ሃይማኖታዊ እምነትን ሳይመረኮዝ ሆኖ መቅረብ አለበት ። ሆኖም የአ ካባቢው ሕዝብ ፍላጎት ተጠንቶ በዚያው መሠረት ፤ ጽሑፎችን ማቅረብ የበለጠ ጠቃሚነት አለው ።

እንዲሁም እንደ ቀበሌው ሁናቴ የመሃይምናን ትምህርት መዘጋጀት አለበት ። ሥርዓተ ትምህርቱ መጀመሪያ ጠቅላላ ዓላማውን ማዘል አለበት ።

ቀጥሎም ፤ ሙያ ነክና ቀለም ነክ በይበልጥ የሚያሰጥበትን ቦታ አይቶ ዝግ ጅት ይደረጋል ፤ መምሪያ ይሰጣል ።

፫/ ሕዝቡ በመማር ምንነቱንና ማንነቱን እንዲያውቅ ለማድረግ ።

፬/ የመሃይምናን ትምህርት ለአገር ዕድገት እንዲውል ፤ በመማሩ ሕዝቡ ራሱን በራሱ እየረዳ የኑሮ አቋሙን እንዲያሻሽል ለማድረግ ፤ የኤኮኖሚው አቋም እንዲዳብር ፤ በአገሩ ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች አውቆ ፤ እሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ እንዲጠቀምባቸው

የማኅበራዊው ኑሮው አቋም እንዲጠነክር ለማድረግ ጤናው እንዲጠበቅ ለማድረግ

የራሱን ፤ የቤተሰቡን ፤ የኅብረተሰቡን መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ ለማ ድረግ ።

፯- ጠቃሚ የሆኑት ብሔራዊ ባህሎች እንዲጠበቁና እንዲስፋፉ ለማድረግ

፰- የአሳብ መለዋወጥ ችሎታው እንዲዳብር ለማድረግ

—ብሔራዊ ቋንቋን በማስፋፋትና በማዳበር

—በመገናኛ ዘዴዎች በሚገባ በመጠቀም ።

—በአገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን ከሌላው ክፍለ ዓለም ጋር የበለጠ የሐሳብ ግንኙነት እንዲፈጥር ፤ እንዲደረጅ በማድረግ ።

፱- የገጠርና የከተማው የጐልማሳውና የሕፃኑ መሃይምናን ፍላጐት የተ ለያየ ስለሆነ ዓላማውም እንደዚሁ መከፈል አለበት ።

—ለከተማው መሃይምን አጠቃላይ የቀለም ትምህርት ይሰጠው ። ማለት ቀለም ነክ ሞያ ትምህርት ።

—ለገጠር መኀይም ግን ሙያ ነክ ትምህርት በተለይም እንደ ግብርና ይሰጠው ።

—ለጐልማሳና ለሕፃናትም መሃይምናን ተገቢ የሆነ ትምህርት ይሰጥ ።

—ለ—

## ለመሃይምናን የሚሰጥ የትምህርት ዓይነት

፩- አማርኛ መናገር ማንበብና መጻፍ

፪- መሠረተ ሂሳብ መለኪያና መሥፈሪያዎች

፫- የቀበሌውን ኑሮና ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል ትምህርት

፬- ኅብረ ትምህርት ሲቢክስ

፭- የግብርና ሙያ ማሻሻያ ቅድሚያ ተሰጥቶት ከቀለም ትምህርት ጋር እንዲጋቡ ማድረግ ።

፮- የዓሣ ማጥመድ ሙያ

፯- ልዩ ልዩ ተግባረ እድ ሙያዎች

፰- የቤተሰብ ኑሮ
፱- ጤና አጠባበቅ
፲- ጠቅላላ ዕውቀት
፲፩- በአካባቢ ላይ በተመሠረተ ሙያ ነክ ትምህርት
፲፪- ሳይንስና ቴክኖሎጂ አዘል መሠረታዊ ትምህርት

—ሐ—

፩- ማንም የተማረ ሁሉ ተነሥቶ ያለመምሪያ መሃይምናንን ለማስተማር የማያዳግተው መሆኑን በመገንዘብ ፤

—ለመሃይምናን መማሪያ መጻሕፍት ፤ ለአስተማሪውም መምሪያ የሚሆን መጻሕፍት ፤ በጥንቃቄ ለየደረጃው እንደአስፈላጊነቱ ተዘጋጅቶ በተቻለ መጠን በነፃ ይታደላል ።

—እነዚህን ጽሑፎች የሚያዘጋጁት ከየሙያው የተውጣጡ ዐዋቂዎች መሆን አለባቸው ።

—መጻሕፍቱ ሲዘጋጁ የሚማረውን የአካባቢውን ሕዝብ ፍላጐትና ችግር አጥንቶ ፤ በዚሁ መሠረት መዘጋጀት አለበት ።

፪- እስካሁን እያንዳንዱ ድርጅት በመሰለው መጻሕፍት እያስተማረ ገን ዘብና ጉልበት ማባከኑ ታውቋል ። ለወደፊት ይህ መባከን እንዳይኖር ፤

—አንድ ሥልጣን ያለው ቋሚ የሆነ ማዕከላዊ የመጻሕፍት ዝግጅት ድር ጅት መመሥረት አለበት ።

—መጻሕፍቱ እንደ የአካባቢው ሁኔታና እንደ ሕዝቡ ፍላጐት በየደረ ጃው መዘጋጀት አለባቸው ፤

—የቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት መታተም አለባቸው ፤

—የተከታታይ ትምህርት መማሪያ መጻሕፍት ማለት በእርሻ ፤ በጤና ፤ በአስተዳደር ፤ በንግድ ወዘተ በመሳሰሉት ላይ የተመሠረቱ መዘጋጀት ይኖር ባቸዋል ።

—የማስተማሪያው መሣሪያዎች ፤ ተማሪዎቹ ከሚያውቁት ዕውቀት ጀምሮ ወደማያውቁት የሚመሩ መሆን አለባቸው ።

—የማስተማሪያ መሣሪያዎች ማለት እንደ ቾክ ፤ ጥቁር ሠሌዳ ፤ ሥዕሎች መብራትና የመሳሰሉት በቀዳሚነት መገኘት ይኖርባቸዋል ።

—የመማሪያ ቦታ እንዲዘጋጅ ያስፈልጋል ።

፫- ሌሎች የማስተማሪያ መሣሪያዎች እንደ ሬዲዮ ፤ ጋዜጣና ቴሌቪዥን የመሳሰሉት በሰፊው እሥራ ላይ ውለው ፤ የሙያ ትምህርት እንዲሰጥባቸው አስፈላጊ ነው ።

፬- መጻሕፍት ሲታተሙ ገንዘብ መጠየቃቸው አይቀርምና ለዚህ ይረዳ ዘንድ ከብሔራዊ አስተባባሪና የመጻሕፍት ዝግጅት ድርጅት ሥር የማተሚያ ቤት መገኘት ይገባዋል ።

፫- ካሁን በፊት የነበሩት በየድርጅቱ የታተሙ መጻሕፍትና መጽሔ ቶቹ ለምርምር ቀርበው ፤ የሚጠቅሙት እየተመረጡና እየተሻሻሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ።

፬- በየሙያው የሠለጠኑ የቋንቋና ሙያ መጻሕፍት የሚያዘጋጁ ሰዎች መደ ልደል ይኖርባቸዋል ።

፭- በሥዕላዊ መግለጫና ፤ ሠርቶ ማሳያ ዘዴዎች ተንቀሳቃሽ ፊልም ፤ ካሴ ቶፍንና ቴፕ በመጠቀም የሙያ ነክ ትምህርትን ማስተማር ዓይነተኛ ዘዴ ነው ።

፮- የመንግሥትና የግል ትምህርት ቤቶች ለመሃይምናን ትምህርት መስጫ ቦታ በቅድሚያ መሰጠት አለባቸው ።

፱- ለሙያ ትምህርት በቂ የማስረጃ መሣሪያዎች እንዲቀርቡ ያስፈልጋል ።

—መ—

## የመሃይምናን ትምህርት ማስተባበሪያ ኮሚሽን

፩- በልዩ ልዩ መንግሥታዊ መ/ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ማለት እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ፤ ብሔራዊ ፊደል ሠራዊትና ሌሎችም የፈጸሙትን መልካም ተግባር በመገንዘብ ፤

—የተደከመበት ሥራ እንዲጠነክርና አጠቃላይ ብሔራዊ ፍሬ እንዲሰጥ በማሰብ ፤

—የመሃይምናን ትምህርት ብዙ ምርምር ፤ ቊጥጥርና ትብብር የሚያስፈ ልገው ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ፤

—ከፍ ያለ ድርጅት ከሥልጣንና ከሙሉ መብት ጋር ስለሚያስፈልገው፤

—ካለፈው የሥራ ልምድ በመረዳት አንድ ራሱን የቻለ አዲስ የመሃይም ናን ትምህርት ኮሚሽን ባስቸኳይ እንዲቋቋምና ይህም በሕግ ታውቆ በአዋጅ የጸና እንዲሆን ጉባኤው አሳስቧል ።

፪- የአስተባባሪው ኮሚሽን ዋና ተግባር ፤

—የመሃይምናንን ጠቅላላ ሁናቴ ለማጥናት

—ዓላማውን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መምህራን ፤ የማስተ ማሪያ መሣሪያዎች ፤ ሥርዓተ ትምህርቱንና እነዚህን የመሰሉትን በኅብረት ለማዘጋጀትና በሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ነው ።

—የመሃይምናን ትምህርት ለመቈጣጠር ።

— ሠ —

## ለመሃይምናን ትምህርት መማሪያ ገንዘብ ማግኛ ዘዴ

፩- የመሃይምናን ትምህርት በፕሮግራምና ጥናት ላይ የተመሠረተ ፕላን እንዲወጣለት ያሻል ። በፕላኑ መሠረት የቱን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ

ታውቆ መንግሥታዊ በጀት እንዲመደብለት ያስፈልጋል ። መሃይምናንን ለማ ስተማር ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ገንዘብ ነው ። ገንዘብ ከሌለ ብዙ ለመሥራት የማይቻል መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለዚህ ቋሚ ሥራ ከተፈለገ ቋሚ በጀት ያስፈልጋል ማለት ነው ።

፪- ለመሃይምናን ትምህርት አገልግሎት እንዲውሉ ታስበው በየመሥሪያ ቤቱ የተደለደለ በጀት በአንድነት ተጠቃሎ የመሃይምናንን ትምህርት በብሔራዊ ደረጃ ለሚመራው ድርጅት እንዲሰጥ ማድረግ ።

፫- እያንዳንዱን መሃይምናን ለማስተማር የሚያስፈልገው ገንዘብ ተተምኖ እስካሁን ከተደለደለው በጀት በላይ ተጨማሪ የሆነውን ገንዘብ መንግሥት እንዲያሟላ ያስፈልጋል ።

፬- ፋብሪካዎች ፤ ኩባንያዎች ፤ ማኅበሮች ፤ ዕድሮችና ሌሎች የግል ድርጅቶች ለመሃይምናን ትምህርት ገንዘብ እንዲሰጡ መገፋፋት ያስፈልጋል ።

፭- እንደ ቀ-ኃ-ሥ- በጎ አድራጎት ፤ ብሔራዊ ሎተሪ ያሉት ድርጅቶች ገንዘብ በማመንጨት ሥራ ተሳታፊ ይሁኑ ።

፮- ቋሚ በጀት ሌላ ገንዘብ ማግኛ ዘዴ ከሕዝብ መዋጮ መሰብሰብ ፤ ከውጭ አገር ርዳታ መጠየቅና በዓላዊ ትርኢት ኤክስፖዚሲዮን ማዘጋጀትና ዕቃና ምልክቶች መሸጥ ነው ።

፯- ቋሚ በጀት የሚያስፈልገው ፤

—በሙያው የሠለጠኑ መምህራንን ለመቅጠር ፤

—የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በሚገባ ለማዘጋጀት ፤ በብዛት ለማሳተምና ለማዳረስ ፤

—የመማሪያ ሥፍራዎችን ለማግኘትና ለማስገኘት ፤

—የመሃይምናን ትምህርት ጥናትና ውይይቶች ለማካሄድ ።

፰- ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዓመት አንድ ጊዜ ፤ የአንድ ቀን ገቢውን እንዲሰጥ ።

፱- ከተባበሩት መንግሥታት ለእንደዚህ ያለው ጉዳይ የሚመጣው ርዳታ በኢትዮጵያውያን የድርጅቱ ኤክስፐርቶች መመራት አለበት ።

—፪—

## ስለመሃይምናን ትምህርት አስተማሪዎች

የመሃይምናን ትምህርት አስተማሪዎች ምን የትምህርት ደረጃና ዕድሜ እንዲኖራቸው የተለየ ጥንቃቄና ውሳኔ ያስፈልገዋል ።

ለዚሁም መምሪያ ይሆን ዘንድ ፤ የሚከተሉትን ጉባኤው አመልክቷል ።

፩- ከ፮ኛ ክፍል በላይ የወጡ ተማሪዎች መሃይምንን የማስተማር ዘዴ ኮርስ ተሰጥቷቸው ፤ ገንዘብ እየተከፈላቸው እንዲያስተምሩ ይደረግ ፤ መደበኛ መም

ህራንም መምሪያ ተሰጥቷቸው እንዲያስተምሩ ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑን ጉባ ኤው ተገንዝቦታል ።

፬- የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፤ የብሔራዊ አገልግሎት ለማበርከት በየጠቅ ላይ ግዛቱ በሚመደቡበት ጊዜ ካሁን ይበልጥ የመሃይምናንን ትምህርት በተጨ ማሪ እንዲያስተምሩ ተግባራቸው መሆን እንዳለበት ጉባኤው አምኖበታል ።

፫- የጦር ኃይሎች ፤ የፖሊስ ሠራዊት ፤ የሃይማኖትና ሌሎች ድርጅቶች በሙሉ ለፕሮግራሙ ተካፋይ ሆነው ማስተማር ይገባቸዋል ።

፬- አስተማሪዎች ከማስተማራቸው በፊት በተለይ ስለጎልማሶች መሃይምን ትምህርት አሰጣጥ መምሪያ ተሰጥቶዋቸው ሲያስተምሩም ቍጥጥር እንዲ ደረግበት ።

፭- በበጎ ፈቃድ አስተማሪዎች ብቻ ከመወሰን ፤ አነስተኛም ቢሆን ቅሉ ፤ አበል ሰጥቶ በዚያው መጠን የማስተማሩን ሥራ ቍጥጥር ማጥበቅ አስፈላጊ ነው ።

፮- የአስተማሪዎቹና የትምህርቱ ፕሮግራም ጥረት በይፋ እንዲታወቅ በመ ጽሔትም ሆነ በሬዲዮ በጋዜጣና ቴሌቢዥን ማሳወቅ ያስፈልጋል ።

፯- ዕጩ መምህራንና ሌሎችም የሙያ ማሠልጠኛ ድርጅቶች የመሃይም ናን የማስተማር ዘዴ እየተሰጣቸው በሚመደቡበት ቦታ ሁሉ የሥራው ተካ ፋይ እንዲሆኑ ።

፰- እያንዳንዱ የተማረ የቤተሰብ ኃላፊ በቤቱ የሚተዳደሩትን መሃይምናን የማስተማር ግዴታ እንዲኖረው ያስፈልጋል ።

፱- ተማሪዎች በየት/ቤታቸውና በየሠፈራቸው የመሃይምናን ትምህርት ጥበብ እያቋቋሙ በሥራው በይበልጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት ያስፈልጋል ።

—ሰ—

## ስለመሃይምናን ተማሪዎች

፩- ጉልማሳ መሃይምናን ተማሪዎች ት/ቤት መጥተው ከተመዘገቡ በኋላ ማቋረጣቸው ታውቋል ። አንዳንዶቹም ትምህርቱ ምን ያደርግልናል በማለት ለመማር አለመፍቀዳቸውን ተደርሶበታል ። ሌሎችም ምክንያቶች የሆኑት በገጠርና በከተማ የመማሪያ ቦታ ፤ የመብራት ፤ መጻሕፍት ፤ መገናኛ ፤ የሠ ለጠኑ አስተማሪዎች እጦትና የመኖሪያ ቤት መራራቅ ናቸው ።

ለነዚህም ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ ከሚችሉት ዘዴዎች ውስጥ ጥቂቶቹ
—የትምህርት ስሜት እንዲያድርባቸው ማድረግ
—ትምህርቱ ከሕይወታቸው ከኑሮአቸው ጋር የተያያዘ እንዲሆን ፤
—የትምህርቱ አሰጣጥ ለነሱ ትርጉም በሚሰጥ ዓይነት እንዲቀርብ ማድረግ
—ሠርቶ በማሳየት በማስተማሪያ ዘዴዎች በመጠቀም

—የትምህርቱን አቀራረብ ዘዴዎች እንደተፈላጊነቱ በየጊዜው ማሻሻል
—አወዳድሮ ሽልማት መስጠት
—ትምህርት የኑሮ ለውጥ የሚያስገኝ መሆኑን ማስገንዘብ ፤
—አስተማሪው ብቻ ሳይሆን ተማሪው የትምህርቱ ተሳታፊ ሆኖ እንዲገኝ ማበረታታት ፤
—መምህራኑም ብቁ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ ይገባል ።

፪- የሴቶች መሃይምናን ቍጥር ከወንዶቹ በጣም የበዛ ሆኖ ይታያል ። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ፤
—ባህል ፤ ሴቶችን ከትምህርት ስለሚያደናቅፉአቸው
—የኤኮኖሚያቸው ሁኔታ ለመማር ስለማይፈቅድላቸው
—ሴቶች ራሳቸው የመማር ጥቅም ስላልተረዱ
—ወላጆችና በተለይም ባሎች ሴት ልጆቻቸውን እንዲማሩ አያበረታቱም ። ስለዚህ ይህ ሁኔታ እንዲሻሻል ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲደረግ ያስፈልጋል ።
—ስለዚህ ሴቶች እንዲማሩ በተለይ ማበረታታት ያስፈልጋል ።

፫- ወንዶችና ሴቶች በአንድነት እንዳይማሩ ባህል በሚያግድበት ቦታ ፤ ሴትና ወንድን ለይቶ ትምህርትን እንዲከታተሉ ማድረግ ነው ።

፬- በዕድሜ አዋቂዎችንና ልጆችን በአንድ ክፍል ማስተማሩ ተገቢ አይደለም ስለዚህ ከ፳ በታች ያሉትን በአንድነት አድርጎ ከ፳—፴ ያሉትን ደግሞ በሌላ ክፍል ፤ እንዲሁም ከ፴—በላይ ዕድሜ ያላቸውን ለብቻቸው ትምህርት መስጠት ይጠቅማል ።

፭- ለመሃይምናን ተማሪዎች አነስተኛም ቢሆን ሽልማት ይሰጣቸው ።

፮- ሁሉ ይማር ከተባለ፤ሁሉን የሚያዝ መንግሥት ስለሆነ፤ መሃይምናን እንዲማሩ የአዋጅ ግዳጅ ሊኖር ያስፈልጋል ።

፯- መሃይምናን የሚያገኙት የምስክር ወረቀት በብሔራዊ ደረጃ ይወሰን ።

፰- መሃይምናን የተማሩትን እንዳይረሱ በቂ ምንባብ የገጠር ቤተ መጻሕፍት እንዲያገኙ በየጊዜው መከታተል ያስፈልጋል ። የገጠር ቤተ መጻሕፍትም ይቋቋሙ ። እንዲሁም የመንደር ጋዜጦች ይዘጋጁ ።

—ሸ—

## የቀለምና የሙያ ትምህርት ስለማገናኘት

፩- ሙያ ሲባል ፤ ሕዝብ ባለው ሥራ ይዞታ ላይ አዲስ ዘዴና ብልሃትን እየተማረ ኑሮውን እንዲያሻሽል ፤ አስተሳሰቡን እንዲለውጥ የሚያደርግ ነው ። ስለዚህ ሕዝቡ የተሰማራበትን ሙያውን በተሻለ ዘዴ መሥራት እንዲችል ዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አዘል በቀለም ትምህርት አማካይነት ይሰጠዋል ማለት ነው ። አሁን ያለው የሚጠቀሙበት ዘዴ እንዴት ያለ እንደሆነ አሳ

ይቶ ከሌላ ከዚህ ከተሻለ ዘዴ ጋር አነፃጽሮ እንዲጠቀምበት ማመልከት ነው ። በመሠረቱ ሙያ ነክነት ያለው የቀለም ትምህርት ይሰጥ ሲባል እያን ዳንዱ ሰው ባለበት ክፍለ ሀገሩ ያለውን ሙያ እንዲያሻሽል እንጂ ፤ ሙያ የለ ውም ማለት አይደለም።ስለዚህ የሚዘጋጁት ጽሑፎች በአካባቢው የሚገኙትን የሙያ ዘዴዎች እየተመለከቱ በተጨማሪ በሌላ ዓለምና ክፍለ ሀገር የተሻሻ ሉትን ዘዴዎች አነፃጽሮ እንዲያቀርብ ፤ ቢደረግ የተሻለ ዘዴ በገዛ ምርጫው ሊቀስም ይችላል ።

፪- ስለዚህ የቀለሙ ትምህርት ይዞታ አዲስ ዘዴና ብልሃት አዘል ቢሆንም መሃይምኑ በየቀኑ የሚያየው ሁናቴ ጋር መያያዝ ይኖርበታል ። ትምህርቱ ቢዘጋጅ ስለ ቀበሌው የሚያውቅ ሰው ያስፈልጋል ።

፫- ሙያ ጠቀሱም ትምህርት በተለይ የእርሻ ልማትን ፤ የዓሣ ሀብትን ተግባረ ዕድን ተከትሎ ሊሰጥ ይገባል ።

፬- በአጠቃላይ አስተሳሰብ ለገጠሬውና ለከተማው የተለያየ የሙያ ነክ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል ። ፕሮግራሞቹን በሁለት ተከፍሎ መን ገድና ዘዴው የተለየ ፤ ዝግጅትም ለተለያየ ዓላማ መሆን አለበት ። በጥንቃቄ የተዘጋጁ የሙያ ነክ መጻሕፍት ሊዘጋጁ በቅድሚያ ያስፈልጋል ።

፭- የሙያ ትምህርት ለመስጠት የሠለጠኑ ሰዎች በብዛት ስለሌለ እር ምጃው አስቸጋሪ ነው ። ስለዚህ ትምህርቱ እያንዳንዱ ሰው የተሠማራበትን ሥራ በተሻሻለ መንገድ እንዲያከናውን ኑሮውን ማሻሻያ አስተሳሰብን መለ ወጫ ፤ ዘዴና መላን መንገሪያ ይሁን ።

## ተጨማሪ ሐሳቦች

፩- ስለመሃይምናን ትምህርት የተደረገው ስብሰባ ጠቃሚ መሆኑን ጉባ ኤው ስለተረዳ ቢያንስ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ተመሳሳይ ጉባኤ እንዲደ ረግ እናሳስባለን ።

፪- ወደፊት በሚደረገው ስብሰባ ላይ ሰፊ አርእስት ከሚቀርብ ይልቅ በተወሰነ አርእስት ላይ ብቻ በመነጋገር ጥሩ ውሳኔ ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል ።

፫- ጠቅላላው ጉባኤ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ተንጠልጥለው እንዳይቀሩ ይህንኑ ጉዳይ የሚከታተል ዘጠኝ አባሎች ያሉበት ኮሚቴ በጠቅላላው ጉባኤ መርጦ አቋቁሞአል ።

፬- ጉባኤው የተወያየበት ሪፖርት ለተካፋዮች እንዲደርስ እናሳስባለን ።

፭- የቀ- ኃ- ሥ- ዩኒቨርሲቲ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመተባበር የመሃይምናን ትምህርት መሪዎችን በማሠልጠንና ፤ ስለ መሃ ይምናን ትምህርት ምርምር በማድረግ ካሁኑ የበለጠ ይካፈል ።

፮- የዚህ ጉባኤ ውጤት ተቀነባብሮ በመጽሔት ላይ ታትሞ ይውጣ ።

፯- በመሃይምናን ትምህርት የተሠማሩት የየድርጅቶቹን ሥራ እንዲያውቁ ፤ የጉብኝት ልውውጥ ያድርጉ ።

፰- አንዱ ድርጅት የሌላውን ሥራ እንዲያውቀውና ፤ ሥራውም አጉል እንዳይደጋገም በአንድ ማዕከላዊ መጽሔት አማካይነት በየጊዜው ዝርዝር መግለጫ ስለድርጅቶቹ ይሰጥ ።

፱- ስለማኅደረ ጥበብ የቀረበው ረቂቅ በሰፊው ተጠንቶ በሥራ ላይ የሚውልበት መንገድ ይታወቅ ።

፲- የትምህርት ሚኒስቴር የመሃይምናን ትምህርት ዲሬክሲዮንን በይበልጥ አጠንክሮ ሌሎችንም እንዲረዳ ማድረግ አለበት ።


The Bottling Company of Ethiopia S. C.




P. O. Box 1346
Addis Ababa,
Ethiopia.




8*

# ግጥም

## የበቀል ዘር

ቱ በል ! ቱ በል ! ማሙሽ ። ቱ !
አለችው እናቱ ፤
ከምጣድ ላይ እየሮጠች መጥታ
ከሚጫወትበት ቦታ ።

o

እናቱ እኩል በኩል ታጥፋ
አፍዋ እስኪነካው አፉን ፣
ያመት ከመንፈቅ ልጅ ፣ የማሙሽን
የልጅዋን ።

መድኃኒት የሚያህል ነገር
ይጫወት የነበር ባፈር ።

o

ሊጥ የነካ እጅዋን ወዳፉ ዘርግታ ፣
በርጋታ
አሁንም አለችው ፣ ቱ በል ! ቱ !
የታባቱ !

ብላ ደረገመችው መሬቱን
አህያውን ፈርተው ዳውላውን ።

o

እሱስ ከሰበሰባቸው ጓሎች
ድቡልቡሎች ፣
አንዱን የነካበት ፣ የጐረቤት ልጅ ነው ።
እና ያስለቀሰው ፣
በኋላም የሮጠው ፣
ካይን የጠፋው ።
በበቀል ልብ
በመቆጨት ፣ በመንገብገብ
ታረገው ብታጣ እናቱ ፣
አሁንም አለችው ፤ ቱ በል ! ቱ !
የታባቱ !

ብላ ደረገመችው መሬቱን
አህያውን ፈርተው ዳውላውን ።

0

በጐረቤት ልጁ ፊንታ
መሬቱ ቢመታ
ማሙሽ ፣ በጣሙን ደስ አለው ፤
ቁጭቱን ተወጣው ።
ዘሩም ሥር ሰደደ
ጨቅላ ልቡን እያለማመደ ።

0

ከዚያን ቀን ጀምሮም ማሙሽ
በየደረሰበት ፤ በመድበሽበሽ
ይጋረፍ ጀመረ በምራቅ አለንጋ
ካናደደው ፣ ሰውም ሆነ ዕቃ ።

0

እና ከቶውን ማን ያውቃል
ዛሬ ፣ በምራቅ አለንጋ ይጋረፋል ።
ለላመት
ወይም የዛሬ ስንት ዓመት ፣
ይሄ የበቀል ዘር ፍሬውን አፍርቶት
በመበቀል መንፈስ ፣ ያጠምቅ ይሆናል ፤
ቂመኛውን በደም ጠበል ።
አይጣል !
አበስት ዘገበረት ያች እናት
ያን ለት ፤
የፈለገች እንትፍ እንዲልላት ።

ሰይፉ መታፈሪያ